# በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማዕ/ጎ/ሀ/ስ ለደብረ ኀይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም ካቴድራል ሰንበት ትምህርት የተሰጠ

## የንግግር ጥበብ ክፍል 1




**አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ**

**(የመጻሕፍተ ሊቃውንት፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)**


**ነሐሴ ፩፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም**

# መንፈሳዊ የንግግር ጥበብ

የንግግር ጥበብ ሐሳብን ለሰሚው በሚስብ መልኩ የማቅረብ ጥበብ ነው፡፡ መንፈሳዊ የንግግር ጥበብ የሚባለው ደግሞ ሰሚውን ለመጥቀም የሚደረግ የትምህርት፣ የምዕዳን፣ የምክር፣ የተግሣጽ...ንግግር ነው፡፡ ዓላማው ሰዎችን መጥቀም ስለሆነ የሰዎችን ስሜት የሚጎዳና ለክፉ የሚያነሳሳ መሆን የለበትም፡፡ ከዚያ ይልቅ የተቆጡትን የሚያበርድ፣ ያዘኑትን የሚያረጋጋ መሆን ይገባዋል፡፡ አንደበት የተፈጠረው እግዚአብሔርን ልናመሰግንበትና ሌላውን ልንጠቅምበት ነውና፡፡ መንፈሳዊ የንግግር ጥበብ መሠረቱ ፍቅር ነው፡፡ "ነገር አዋቂ አንደበት ወንድሜ ወንድሜ ማለትን ያበዛል፡፡ በጎ አንደበት ወዳጅን ያበዛል እንዲል (ሲራ.6፥5)፡፡ ለሌሎች እንደሚጠቅም ለመግለጽም "መፈውስ ልሳን ዕፀ ሕይወት ውእቱ" ይላል (ምሳ.17፥4)፡፡ መንፈሳዊ የንግግር ጥበብ ሌሎችን የምናድንበትና የእግዚአብሔርን ሥራ የምንገልጽበት ነው፡፡ መልካም ንግግር ሕይወት ሲሆን ክፉ ንግግር ሞት ነው፡፡ "ሞት ወሕይወት ውስተ እደ ልሳን" እንዲል (ምሳ.18፥21)፡፡ በጎ ንግግህ ሰውን ደስ እንደሚያሰኝም "በጎ አንደበት ደስ ያሰኛል" ይላል (ሲራ.40፥21)፡፡ የክፉ ሰው ንግግር ግን አጥንትን ይሰብራሀ (ሲራ.28፥17)፡፡ መንፈሳዊ የንግግር ጥበብን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንማራለን፡፡ ከምንም በላይ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ንግግር ዋና መሠረታችን ነው፡፡ ስለእርሱ ወንጌላዊው ሉቃስ "ወእለ ሰምዕዎ ኵሎሙ አንከሩ ሞገሰ ቃሉ ወሣዕሣዐ አፉሁ" ብሏል (ሉቃ.4፥22)፡፡ በመንፈሳዊ የንግግር ጥበብ ውስጥ መሠረታዊ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ሞገሰ ቃል (የቃል መወደድ)
- ጣዕመ ነገር (የነገር ጣዕም)
- ሣዕሣዐ አፍ (የአንደበት ቅልጥፍና)

ጣዕመ ነገር የሚባለው የሐሳባችን ፍሬ ነገር ነው፡፡ ሞገሰ ቃል የሚባለው ጣዕመ ነገርን የምናስተላልፍበት ቃል መወደድ ነው (የተመረጡ ቃላትን መጠቀም) ነው፡፡ ሣዕሣዐ አፍ እጅግም ሳይዘገዩ እጅግም ሳይፈጥኑ መካከለኛ በሆነ መልኩና ለሰሚ ግልጽ በሆነ መልኩ ንግግርን ማቅረብ ነው፡፡

## የመንፈሳዊ ንግግር ጥበብ መርሖዎች

- ማወቅ፡- ልንናገረው ስላሰብነው ነገር ግንዛቤ ከሌለህ ንግግራችን ግልጽ ያልሆነና ሰሚን የሚያሰለች ይሆናል፡፡ ስለዚህ መጀመሪያ ጉዳዩን በደንብ ማወቅ ይቀድማል፡፡
- የቋንቋ ዕውቀት መኖር፡- ምንም እንኳ ስለአንድ ነገር ግንዛቤ ቢኖረንም ያንን የተገነዘብነውን ነገር ለሌሎች ሰዎች ለመግለጽና ለማብራራት የቋንቋ ዕውቀት አስፈላጊ ነው፡፡
- የሰሚን ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዝንባሌ መለየት፡፡
- የንግግሩን ዓላማ መለየት፡- የመንፈሳዊ ንግግር ዋና ዓላማ የእግዚአብሔርን እውነት መመስከርና ሰዎችን መጥቀም ነው፡፡
- ንግግራችንን ቅደም ተከተል ማስያዝ
  -መግቢያ፡- የሰማዕያንን ትኩረት የሚስብ ኀይለ ቃል፣ ጥያቄ ወይም ጉዳይ ማቅረብ
  -መካከል፡- ንግግራችንን በምሳሌዎች፣ በታሪኮችና...ወዘተ ከፋፍሎ ማቅረብ
  -ማጠቃለያ፡- ዋናውን መልእክት ከእኛ ሕይወት ጋር አዋሕዶ አሳጥሮ መግለጽ

- ምሳሌዎችንና ታሪኮችን መጠቀም፡- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር በእርሻ፣ በእርሾ፣ በእረኞችና በመሳሰሉት እየመሰለ ያስተምር ነበር፡፡
- እይታችንን ሁሉን ያማከለ ማድረግ፡- ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ አለማየት፣ ፈገግታ ያልተለየው ገጽ መኖር፣ የአካል እንቅስቃሴያችንንና ነገራችንን ማዋሐድ፡፡
- መለማመድ፡- ብዙ ሰዎች ጥሩ ተናጋሪ የሆኑት በልምምድ፣ በመማር፣ በማንበብና በመሳሰለው ነው፡፡ በተማሪነቱ ጊዜ ጌታን ከሰማይ እሳት አውርዶ ሰዎችህ እንዲያጠፋ የጠየቀ ዮሐንስ ከተማረ በኋላ ግን ሮምናን ለማዳን በእሳት አንዳጅነት እስከማገልገል ደርሷል፡፡ ትምህርት አመለካከትን፣ አነጋገርን ይለውጣልና፡፡
- ዝግጅት ማድረግ፡- ይህ ዝግጅት ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ ከምናደርጋቸው ዝግጅቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

  -ስለምናወራው ነገር በቂ ዕውቀትን ከመጻሕፍት፣ ከሰዎች፣ ከልምዳችን…መሰብሰብ

  -ንግግራችንን እንዴተ እንደምናቀርበው የአነጋገር፣ የእንቅስቃሴ፣ የሰዓት፣ የዓረፍተ ነገር አወቃቀር ዘዴዎችን መለማመድ

  -ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን አስቀድማችሁ መገመትና ሊያጋጥሙ ለሚችሉ ችግሮች ቅድመ መፍትሔዎችን ማዘጋጀት፡፡
- ፍርሀትን ማስወገድ፡- የምንናገረው ጉዳይ እስካለን ድረስ ማንንህ ሳንፈራና ሳናፍር ጉዳዩን መናገርና መግለጽ ይገባናል፡፡ ምንም እንኳ ከመድረኩ በጣም የተከበሩ ሰዎች ነገሥታት፣ ጳጳሳት፣ ምሁራን…ቢኖሩ ልናቀርበው ያሰብነውን ጉዳይ በድፍረት ማቅረብ አለብን፡፡ ልንናገረው ካለው ነገር ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ ይገባናል፡፡ ሰዎች ምን ይሉኛል በማለት በሰዎች ድርጊት ላይ የተመሠረተ አቀራረብን ማስወገድ ይገባናል፡፡
- ድግግሞሽንና ተመሳሳይነትን ማስወገድ፡- የሰው ልጆች የተደጋገመ ነገር ብዙ ጊዜ ያሰለቸናል፡፡ ስለዚህ የሐሳብ ድግግሞሽን፣ የአቀራረብ ድግግሞሽን ማስወገድ አለብን፡፡ አንድ ዓይነት አበቦች ካሉበት የአትክልት ቦታ ይልቅ የተለያዩ አበቦች ያሉበት የአትክልት ቦታ ለተመልካች ሳቢ ነው፡፡ ከተደጋጋሚ ሐሳቦችና አቀራረቦች ይልቅ ያልተደጋገሙ ሐሳቦችና አቀራረቦች ለሰሚው ሳቢ ናቸው፡፡
- ሐሳብን ማደራጀት፡- ከተበታተኑ ሰዎች ይልቅ በአንድነት ያሉ ሰዎች አቅም አላቸው፡፡ ከተበታተነ ሐሳብ ይልቅ የተደራጀ ሐሳብ ሰሚውን የመሳብ አቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡
- የድምፁት ልምምድ ማድረግ፡- ሐሳባችንን ለመግለጽ የምንጠቀማቸውህ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮች በትክክለኛ የአገባብ ስልት ለማንበብ መለማመድ አለብን፡፡ አለበለዚያ ማክሰኞ ለማለት ማስከኞ ልንል እንችላለን፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ሰሚውን ወደ ንቀት ሊያመራው ይችላል፡፡ አነጋገራችን እኛን ራሳችንን ሊመስል ይገባል እንጂ የሌላ ሰዎችን ድምፀት ለመጠቀም ብለን ችግር ውስጥ መግባት የለብንም፡፡ የድምፅ ፍጥነትን እንደ አስፈላጊነቱ መቀያየር ይገባል፡፡ ይህ የሰሚውን ትኩረት ለመሰብሰብ ይጠቅማልና፡፡
- አለመቸኮል፡- በጣም ዝግ ማለት ሰሚን እንደሚያሰለች ሁሉ በጣም መፍጠንም ልናስተላልፈው የፈለግነውን ሐሳብ ቀጥታ ወደሰሚዎች እንዳይደርስ ያደርጋል፡፡ በየንግግራችን መካከል አጭር ዕረፍት ማድረግ ካለብንም ማድረግ ይገባናል፡፡
- ማወዳደር፣ ማነጻጸር፣ ልዩ ልዩ ዘይቤዎችን መጠቀም፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን መጠቀም፡- ይህ ለምናስተላልፈው መልእክት ጉልበትን ይሰጠዋል፡፡ ለምሳሌ ቅዱሳን አይፈሩም ብለን ከመናገር ይልቅ ቅዱሳን እንደ አንበሳ ደፋሮች ስለሆኑ አይፈሩም የሚለው አገላለጽ በሰሚው ዘንድ ተጽእኖ ፈጣሪነቱ ከፍ ያለ ነው፡፡

- በራስ መተማመን፦ ንግግራችንን ለአብሮ አደግ ጓደኞቻችን እንደምናወራ አድርገን ሳንፈራና ሳናፍር ማቅረብ አለብን። ስለጉዳዩ በቂ ዕውቀት መኖርና በቂ ልምምድ ማድረግ በራስ መተማመንን ከፍ ያደርጋል።

## የንግግር ጥበብ ጥቅሞች

- እውነትን ለሰሚው በትክክል ተደራሽ ለማድረግ
- ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለንን መልካም ግኑኝነት ለማሳደግ
- ሌሎች ሰዎችን ለመምራት፣ ለማሳመን፣ ለማነሳሳት። እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርታቸው እስከዛሬ ተወዳጅ የሆነውና የማሳመን አቅማቸው ትልቅ የሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ርዳታ በተጨማሪ የንግግር ጥበብን ተምረው በማወቃቸው ነው።

ንግግራችን ለሰሚው ተወድዶ ይቀርብ ዘንድ የሰሚውን ፍላጎት፣ ምኞት፣ ስሜት…የሚገልጽ መሆን አለበት። ከቅዱስ ጳውሎስ የማስተማር ዘዴዎች አንዱ ለአይሁድ እንደ አይሁዳዊ፣ ለአረማዊ እንደ አረማዊ ሆኖ ማስተማሩ ነው። ማንነትን ሳይለቁ ሌሎችን መሆን ስሜትን መጋራት ነውና። ሌላው በንግግር ጊዜ ልናስተውለው የሚገባን ነገር ሸምድዶ ከማቅረብ ይልቅ ተረድቶ ማቅረብ የተሻለ መሆኑን ነው። በንግግራችን መካከል መቆራረጥ እንዳይኖር እንደ አስፈላጊነቱ ዋና ዋና ሐሳቦችን የያዘ ትንሽ ማስታዎሻ ቢኖረን መልካም ነው። የምንናገረው ሐሳብ ከሌለን ግን ዝምታ ይሻለናል።